# ዜና ኢዴኃኅ

በኢዴኃኅ የሕዝብ ግንኙነትና የማስታወቂያ ኮሚቴ
በየወሩ እያተዘጋጀ የሚወጣ የዜና መጽሔት

ልዩ እትም ቁጥር 2 ነሐሴ ፲፱፻፺፯


## ርዕሰ አንቀጽ

## የሕዝብ ድምፅ ይከበር!!!

አዎን – በቆሎ ከጤፍ ዱቄት የሚወጣ አይመስለውም:: የሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥርዓት ላለፉት አስራ አምስት ዓመታት በሁሉም መስክ ከኔም ወዲያ ላሳር ሲል፥ ከምንም በላይ ራሱን አተልቆ ሲመለከት፥ በሕግ ሳይሆን በጠመንጃና በጉልበት ሲያስተዳድር ነው የኖረው:: ግንቦት ሰባት 1997 ዓ.ም. ግን በማንአለብኝነት ከመጠን በላይ ሰግጎ የነበረው አንገቱ ዘመመ፥ አሳንሶ ይመለከተው የነበረው ሕዝብም ኃያልነቱን በገሃድ አሳየው:: አዎን– በቆሎ ከጤፍ ዱቄት የሚወጣ አይመስለውም::

ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም እንዲሉ ማንአለብኝነትና አምባገነንነት የተጠናወተው ሥርዓት የሕዝብን ኃያልነት አሻፈረኝ ብሎ የተለመደውን የጦር ሰይፉን መዝዞ እንደተናንቱ ሁሉ በንፁኃን ዜጎች ደም ለመታጠቡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የደረሰው እልቂት በቂ ምስክር ነው:: ከምርጫው በኋላም ሆነ በፊት የተከሰተው ጭፍጨፋ ምክንያት የሥርዓቱ ቁንጮዎች እንደሚያመካኙት " የአደገኛ ቦዘኔዎች " ወይም " የዘራፊዎች" ድርጊት አልነበረም:: ይልቁንም በግንቦቱ ምርጫ ሂደት የኢትዮጵያ ሕዝብ በማያሻማ ቋንቋ ለውጥ ፈላጊነቱን እንዲሁም ወገንተኝነቱን በተቃዋሚ ጎራ ለተሰለፉት ሁሉ በግልፅ ያሳየበት ዕለት ነውና "የሕዝብ ድምፅ ይከበር!!!" ብለው ፋና ወጊ ሆነው የወጡ ዜጎች በግፍ የተጨፈጨፉበት ታሪካዊ ክስተት ነው::

እጅጉን የሚገርመው ለሕዝብ ድምፅ መከበር ክቡር የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉ ዜጎች ደም ሳይደርቅ እያከታተለ ከሥርዓቱ አምባ የሚዘንበው የግፍ ጎርፍ በምርጫው ወቅት በጉልህ ብልጫ የተሸነፉትን የሥርዓቱን ቱባ ቱባ ባለሥልጣናት ሳይቀር መልሶ አሸናፊ በማድረግ አስቂኝ ትርዒት ተጠናቀቀ ኢዴኃኅ ቀደም ሲል አበክሮ በሌላ ገለልተኛ ኃይል እንዲተካ ይጠይቅ የነበረው የአገዛዙ ምርጫ ቦርድ የሕወሓት/ኢሕአዴግን አሸናፊነት በገሃድ አውጇል:: ዓይኔን ግንባር ያርገው ካልተባለ በስተቀር ያለጥርጥር በአደባባይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ተሰርቋል:: እየሞገተን የሚገኘውና እልባት የሚሻው የወቅቱ ጥያቄ የሕዝብ ድምፅ ሲሰረቅ ለሕዝብ ዘብ ቆመናል የሚሉ ድርጅቶችና ወገኖች ሚና ምን መሆን አለበት? የሚለው ነው::

ያለማጋነን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ታሪክ ሂደት እንዳለንበት ወቅት እጅግ ፈታኝ ጊዜ ላይ ደርሰን አናውቅም ማለት ይቻላል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በነባር አኩሪ ባህሉና ወጉ ሥርዓትና ትዕግስትን በተላበሰ መልኩ ያለፍርሃት ድምፁን ከፍ አድርጎ በቃኝ ብሎ ምርጫውን በገሃድ አሳይቷል:: በዚህም ታሪካዊ ኃላፊነቱንና የዜግነት ግዴታውን ለመወጣቱ ምስክር አያስፈልገውም:: " ፈረንጅ አምላኩ " የሆነው ሥርዓት በታዛቢነት ያስገኛቸው

የውጭ ተመልካቾች ብቻ ሳይሆኑ አገዛዙን ራሱን መልሶ እስኪገርመው ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደፋርና ቆራጥነቱን ለቀጣይ ትውልድ አርኣያ በሚሆን መልኩ አኩሪ ታሪኩን ዳግም አድሷል:: ከኢትዮጵያ ሕዝብ መወለድን የሚያኮራ የሚያደርገው በራሱና በአገሩ የሚመጣን ለመጋፈጥ ያለማወላወሉ ብቻ ሳይሆን የሞትን ድንበር ጭምር ለመግፋት ሁሌም ዝግጁ መሆኑ ነው::

ይኸንን አኩሪ ሕዝብ ከምርጫው በፊትም ሆነ በኋላ ለራሱ የሥልጣን ባለቤትነት መረጋገጥ ይረዳ ዘንድ ድምፁ-ውሳኔውን ለተቃዋሚ ወገኖች  እንዲሰጥ በውድድሩ የተሳተፉ የፖለቲካ ድርጅቶች÷ የሙያና የሲቪክ ማኅበራት÷ አገር ወዳድ ታዋቂ ግለሰቦችና ምሁራን አበክረው የመጠየቃቸውን ያህል ዛሬ ድምፁ ሲሰረቅም ከጎኑ ተሰልፈው የተሰረቀው ድምፁ ይመለስ ዘንድ በጋራ መቆምና መታገል ይጠበቅባቸዋል:: ኢዴኃኅ የዛሬውን ፈተና በአንድነትና በወንድማማችነት/እህትማማችነት መንፈስ በጋራ እምነትና ውሳኔ ለመወጣት ሳንችል ከቀረን ትልቁንና ዋናውን የሕዝባችንን አመኔታ ማጣት ብቻ ሳይሆን ለቀጣይ ግፍና መከራ ራሳችንን የምናመቻች  መሆኑን በፅኑ ያምናል::

እንደሚታወቀው ኢዴኃኅ ገና ከመሠረቱ ምርጫው ነፃና ፍትኃዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅና ዓለም- አቀፍ የምርጫ ሕጎችን የተከተለ እንዲሆን መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች አቅርቦ በሥልጣን ላይ ካለው መንግስት ጋር ቀጥተኛ ድርድር ውስጥ በመግባት አንዳንድ የምርጫ ሕጎች እንዲሻሻሉ ለማድረግ ቢቻልም የምርጫ አስፈፃሚዎችንና የምርጫ ቦርዱን በገለልተኛ አካል የመተካቱ ጥያቄ በአምባገነኑ አገዛዝ አሻፈረኝ ባይነት ሳይሳካ ቀርቷል:: የቅድመ ሁኔታዎቹ መሟላት ፖለቲካዊ ፋይዳ ዛሬ እንዲህ ፍንትው ብሎ ሊታይ በወቅቱ እንደ እናቴ ቀሚስ ጠለፈኝ ምክንያት ተደርጎ መታየቱን ከቶም አንዘነጋውም::
ነፃና ፍትኃዊ ምርጫ ከተካሄደ ገዥው ፓርቲ እንደልቡና አሁን እንደታየው ግልጽና ዓይን ያወጣ የጠራራ ፀሐይ ዘረፋ ማድረግ እንደማይችል እርግጠኞች ስለነበርን ዋናውን ትኩረታችንን ለምርጫው ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት በማድረጋችን  ምርጫውን እንደ ትግል ስልት እንጂ እንደ ዓላማ አልተመለከትነውም:: ለዚህም የኋላ ኋላ የሕዝባችንን ለትግል ቆርጦ መነሳት በማየትና የትግሉን ቀጣይነት በማስተዋል በጥቂት ጊዚያት ዝግጅት ወደ ምርጫው ገብተን ባደረግነው ተሳትፎ ዋጋ ከፍለንበታል:: ነገር ግን በደጋፊዎቻችን በአባሎቻችንና በተለይም በምርጫ አስፈፃሚዎቻችንና በምርጫ እጩዎቻችን ያላሰለሰ ብርቱ ጥረት የሚጠበቅብንን ያህል ባይሆንም ባገኘነው ውጤት ሕዝባችን እንደሌሎች ሁሉ በኛም ላይ አደራውን መጣሉን በግልፅ ተረድተናል:: " አደራ በላ " መባል ደግሞ በአገራችን ሕዝብ ዘንድ ከቋጥኝ የከበደ ስድብ ነውና ዛሬ የሕዝባችን ድምፀ ውሳኔ በአደባባይ በአምባገነኖች ሲነጠቅ እጃችንን አጣምረን አንመለከትም::

የአገራችንን የወደፊት ዕድል ለመወሰን ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ዛሬ በጋራ በወንድማማችነት/እህትማማችነት እና በአንድነት መነሳትና የጋራ መፍትሔ መሻትን ስለሚጠይቅ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በተደረጉ ሁለት ታሪካዊ ጉባዔዎቻችን የደረስንባቸውን አቋሞች እነሆ ለማለት ተገደናል:: ጥሪያችን ለዴሞክራሲያዊ ለውጥና ለሕዝብ መብት መከበር ለቆሙ የፖለቲካ ድርጅቶች÷ ለአገራችን ዴሞክራቶች÷ ለሲቪክ ማኅበረሰቡ አባላት÷ ለሙያ÷ ለሠራተኞች÷ ለገበሬዎች÷ ለወጣቶች÷ ለተማሪዎች÷ ለሴቶችና ለሌሎች ድርጅቶች ብሎም ለትግሉ ዋነኛ ባለቤት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሆን ዓላማችንና ግባችን <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ይከበር</u> ነው::

## <u>የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ( ኢዴኃኅ ) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወዳዳሪዎች ጉባዔ የአቋም መግለጫ</u>

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) በግንቦት ፯ ቀን ፲፱፺፯ ዓ/ም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅብረቱን ወክለው ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች ጋር የሁለት ቀናት ጉባዔ

(ሐምሌ ፴ ቀን እስከ ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም) በአዲስ አበባ የብሔራዊ ሎተሪ አዳራሽ አካሂዷል፡፡ ጉባዔው ኀብረቱ በተወዳደረባቸው ክልሎች በምርጫው ዙሪያ የነበረውንና ያለውን ሁኔታ በሚመለከት በየክልሎቹ የቀረቡ ሪፖርቶችን በማድመጥ ስለ ምርጫው ሒደት የልምድ ልውውጥ አድርጓል፡፡

በተጨማሪም ጉባዔው በኀብረቱ አመራር የተዘጋጁትን ማለትም የጉባዔውን የመወያያ ሰነድ፥ አማራጭ የድርጊት ፕሮግራም፥ የኀብረቱን መለስተኛ የፖለቲካ ፕሮግራምና ከቅንጅት ጋር በመሆን ስለ ሽግግር ጥምር መንግሥት ምስረታ ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትርና የኢሕአዴግ ዋና ፀሐፊ ለአቶ መለሰ ዜናዊ የተፃፈውንና በይዘቱ ላይ ገለፃ የተደረገበት ደብዳቤ ቀርቦ ውይይት አድርጎባቸዋል፡፡

ጉባዔውም በውይይቱ ኀብረቱ ወደ ምርጫ የገባው ሕወሓት/ ኢሕአዴግ በለመደው መንገድ መራጩን ሕዝብ ለማስፈራራት፥ ለማዋከብና ለማፈን መዋቅሩን አጠናክሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ወርዶ መንቀሳቀስ ከጀመረ ከዓመት በላይ ባስቆጠረበት፥ በአብዛኛው የምርጫ ክልሎች በተለይም በገጠር አካባቢዎች ሚዲያና ገለልተኛ ታዛቢዎች በሌሉበትና ባለው ኃይሉ ተጽዕኖ ለማሳረፍ ክፍት በሆነበት፥ ኢዴኃን ወደ ምርጫው ለመግባት ዘግይቶ በወሰነበትና በምርጫው ዝግጅት የድርጅታዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ ውስንነት ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም ተወዳዳሪዎቻችን፥ ካድሬዎቻችንና የምርጫ ታዛቢዎቻችን በልበ-ሙሉነትና ቆራጥነት እስከ ሕይወት መስዋዕትነት በጠየቀ ትግል ያስመዘገቡት ውጤት የሚያበረታታ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡
መገናኛ ብዙኃን ለምርጫ ቅስቀሳ ሥራ መፈቀዱና በተለይ በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚዎች መካከል የተደረጉ ክርክሮች በራዲዮና በቴሌቪዥን መተላለፉቸው ለተደረገው ፉክክርና ለተገኘው ውጤት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረጉን ጉባዔው አጢኗል፡፡

ይኸ ፉክክርና ውጤት ሕወሓት/ኢሕአዴግ ለዘመናት የተቃዋሚዎችን ሰላማዊ ትግል ለማንኳሰስ ሲያሰማ ለነበረው "ጠንካራ ተቃዋሚ ስጠን" የሚለው የይስሙላ ፀሎት እና ሰማንያ አምስት ከመቶ የገጠሩ ሕዝብ ከኔ ጋር ነው ለሚለው የዘወትር ፕሮፖጋንዳው በቂ ምላሽ መሰጠቱን አረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ሕወሓት/ኢሕአዴግ ራሱን አግዝፎ በሚያሳየው መነፅር ብቻ እየተመለከተ በምርጫው ሽንፈት ቢያጋጥመኝ ብሎ ከማሰብ ከከለለው ግርዶሽ ውስጥ ለመውጣት ባለመቻሉ፥ በሥልጣን መቆየትን "የሞት ሽረት ጥያቄ" አድርጎ ስለሚመለከት ሕዝቡ በድምፅ የሰጠውን ውሳኔ ለመቀበል ባለመዘጋጀቱ ከምርጫው ዕለት (ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም) ጀምሮ የአልሞት ባይ ተጋዳይ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ድርጊት ውስጥ መግባቱን ጉባዔው አጢኗል፡፡

ይኸ ሁኔታ አገራችንን ወደ ትርምስ ከመግፋት በተጨማሪ በጅምር ላይ ያለውን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጥረት ሊያመክነው ይችላል የሚል ስጋት በሕዝባችንና በዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ መፈጠሩንም ጉባዔው ተረድቷል፡፡ የምርጫውን ጉድለት ለማጣራት የተደረገው እንቅስቃሴ አለመሳካቱንና በአሳዛኝ ሁኔታ ለኢሕአዴግ ተጨማሪ "ውጤት" ለማስገኘት የተደረገ እንቅስቃሴ ብቻ ሆኖ መምከኑን ጉባዔው ተገንዝቧል፡፡

በመሆኑም ጉባዔው ከላይ የደረሰባቸውን ጭብጦች መሠረት በማድረግ ለሕዝባችን፥ ለሕወሓት/ኢሕአዴግና ለዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ ስጋት ምላሽ የሚሰጥ አማራጭ ማቅረብ እንዳለበት ተገንዝቧል፡፡ ለዚህም አገራችንን ከቀውስ ለመታደግ የሚያስችል፥ ሕዝባችን የጣለብንን አደራና ያሳደረውን አመኔታ ያገናዘበ፥ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችልና አንድ አሸናፊ ነኝ ባይ ፓርቲ የሌለበት አስታራቂ የመፍትሔ አሳብ እና ተፈጻሚነቱን የሚያመለክቱ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ የጉባዔው ተሳታፊዎች በአንድ ድምፅ አውጥተናል፡፡

## I. የኅብረቱን ውስጣዊ አደረጃጀትና እንቅስቃሴ በተመለከተ፤

1.1 ኅብረቱ ከተመሠረተ አጭር ጊዜ ቢሆንም ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች የሚያበረታቱ መሆኑን ጉባዔው ግንዛቤ አግኝቷል። ይሁን እንጂ አገራችን ካለችበት ሁኔታና ሕዝባችን ከሚገኝበት የፍትኅና የዴሞክራሲ እጦት እንዲሁም አሳዛኝ የድህነት አረንቋ አኳያ እጅግ ብዙ ተግባራት ከፊታችን የተደቀኑ ስለሆነ ኅብረቱ በሁሉም ዘርፍ እራሱን አጠናክሮ ሕዝባችንን ለማናቸውም የትግል ጥሪ ማንቀሳቀስ በሚችል ሁኔታ ላይ እንዲገኝ እንዲደረግ፤

1.2 በግንቦቱ ምርጫ ውስጥ የገባነው ዘግይተን መሆኑ የታወቀ ቢሆንም ባለችን አጭር ጊዜ ውስጥ የተደረገው ጥረት አበረታች መሆኑን ጉባዔው አጢኗል። ይሁን እንጂ ባለው የገንዘብና የማቴሪያል አቅም ማነስ ለቅስቀሳ ሥራ እጅግ መጠናከር ሲኖርብን ከማስተባበር ጉድለቶች የተነሳ የተፈለገውን ያህል ያልተንቀሳቀስን ስለሆነ ይኸ ለወደፊቱ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲታረም፤

2.3 በውጭ ያሉ አባል ድርጅቶችና አባሎች የውጭውንና የአገር ቤቱን ጽ/ቤት በገንዘብና በማቴሪያል በመደጎም፥ እንዲሁም የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ በማድረግ ያከናወኑት ተግባር የሚያበረታታ መሆኑን ጉባዔው ተረድቷል። ይኸ አሁንም ይበልጥ ተጠናክሮና ዳብሮ እንዲካሄድ እንዲደረግ ጉባዔው ጥሪ አድርጓል።

## II. የ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ምርጫና ከዚያ በኋላ የተከሰቱ ሁኔታዎችን በተመለከተ፤

2.1 የ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ምርጫ በአገራችን የዴሞክራሲ ጭላንጭል መታየት የሕዝብን ተሳትፎ ምንነት በገሃድ ያሳየ፥ ዓለም ያደነቀው ሕዝባዊ ተሳትፎ የነበረበት እንደነበር ይታወቃል። ኅብረቱ ዓለም-አቀፍ የነፃ ምርጫ መስፈርቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ እንኳ ቢሆን በሂደቱ ውስጥ በሙሉ ልብ ገብቶ ለመሳተፍ ያደረገው ውሳኔ ትክክል መሆኑን ጉባዔው ያረጋግጣል።

2.2 ሕዝባችን በነቂስ ወጥቶ ሕዝባዊ አመኔታ የሌለውን የወያኔ/ ኢሕአዴግ መንግሥት በካርዱ ከጣለ በኋላ ይኸ መንግሥት በለመደው የማጭበርበር ስልቱ ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚያደርገውን ሩጫ ጉባዔው በአንድ ድምፅ እያወገዘ፥ ይኸ ሁኔታ ተገትቶ፥ የሕዝባችን ድምፅ ተከብሮ በአገራችን ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር ጉባዔው በአጽንዖት ይጠይቃል።

2.3 ኅብረቱ የቀረበው ተኣማኒነት ያለውና በገለልተኛ አካል ማጣራቱ እንዲካሄድ የሚለው አሳብ ለምርጫው ውጤት መቋጨት ትክክለኛ አማራጭ ስለሆነ ገዥው ፓርቲ ይኸንን አሳብ ተቀብሎ የሕዝባችንን ድምፅ እንዲያከብር ጉባዔው ይጠይቃል።

2.4 ከምርጫው ጋር በተያያዘ በመላው አገሪቱ በአጠቃላይና የገዥው ፓርቲ ቱባ ቱባ ካድሬዎች በተለይ በተሸነፉባቸው አካባቢዎች እየተካሄደ ያለው ወከባ፥ እስራት፥ ግድያና ማሳደድ በአስቸኳይ ቆሞ፤ በሕዝባችን ላይ የሚካሄደው የበቀል እርምጃም ተገትቶ፤ ሕዝባችን ሰላማዊ ሕይወቱን እንዲመራ ገዥው ፓርቲ አስቸኳይ የእርምት እርምጃ በመላ አገሪቱ እንዲወስድ። ከዚህ ጋር በተያያዘ የገዥውን ፓርቲ የሥልጣን ዕድሜ ለማራዘም ፓርቲውና መንግሥት ሕዝቡን ለከፋፍለህ ግዛ ሴራቸው በሐይማኖትና በብሔር የመከፋፈል እንቅስቃሴቀቸውን በአስቸኳይ እንዲያቆሙ፤

2.5 በሕዝብ ድምፅ የተሸነፉት ቱባ ቱባ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናትን በኋላ በር መልሶ በሥልጣን ላይ ለማስቀመጥ የሚደረገው ሕገ-ወጥ ሩጫ በአስቸኳይ ቆሞ የሕዝቡ ድምፅ እንዲከበር፤

2.6 ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸውን በመጠቀም የኅብረቱ አባል ድርጅቶች አባል በመሆናቸው ከሥራቸው የተባረሩ ሁሉ በአስቸኳይ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ደመወዛቸው ተከፍሏቸው ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ፤

2.7 የሕዝባችንን ድል ሳናስነጥቅ ለአገራችንና ለሕዝባችን ደኅንነት ተብሎ በኅብረቱና በቅንጅቱ የቀረበው የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ፅንሰ-አሳብ ተቃዋሚ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎችን የአመራር ብስለትና የኃላፊነት ስሜት የሚያረጋግጥ በመሆኑ ይኸ ወርቃማ አማራጭ ጊዜ ሳይሰጠው በኢሕአዴግ ተቀባይነት አግኝቶ እንዲተገበር ጉባዔው በመላው የአገራችን ሕዝብ ስም ጥያቄውን ያቀርባል። መላው የአገራችን ሕዝብም ለሚደረግለት ጥሪ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት እንዲዘጋጅ ጉባዔው ጥሪውን ያቀርባል።

2.8 የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ምስረታን ኢሕአዴግ እንዲቀበል የኢትዮጵያ ወዳጅ አገራት፥ ዓለም-አቀፍና አህጉራዊ ተቋማት የበኩላቸውን ተፅዕኖ እንዲያደርጉ ጉባዔው ጥሪውን ያቀርባል።

2.9 ገዥው ፓርቲ ይኸንን የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ምስረታ ካልተቀበለና በማጭበርበር ከገፋበት ኅብረቱ መላ አባላቱን በማንቀሳቀስ በሕገ-መንግሥቱ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉትን የሰላማዊ ትግል ስልቶች በመጠቀም የሕዝባችንን ትግል አፋፍሞ እንዲቀጥል በሙሉ ድምፅ ተስማምተናል።

2.10 ወያኔ/ኢሕአዴግ ከግንቦት ሰባቱ ሕዝባዊ ፍርድ በኋላ በመላ አገሪቱ ባሉ ክልሎች ሁሉ ሠራዊት አሰማርቶ የሕዝባችንን ሰላምና መረጋጋት የሚያውኩ ተግባራትን እየፈፀመ መሆኑን ጉባዔው ከየክልሉ ከቀረቡት ዘገባዎች ተረድቷል። የአገር መከላከያ ሠራዊትን ምንም ዓይነት የሰላም መታወክ በሌለበት ሁኔታ ከጦር ሰፈር (ካምፕ) አውጥቶ ሕዝብ ውስጥ ማሰማራት የሕዝቡን ሕገ-መንግሥታዊ መብት መጋፋት ስለሆነ ሠራዊቱ ባስቸኳይ ወደ ጦር ሰፈሩ (ካምፕ) እንዲገባ ጉባዔው አበክሮ ይጠይቃል፤

2.11 የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ለግንቦት ሰባቱ ምርጫ የውጭ ታዛቢዎች እንዲገቡ ባካሄደው ድርድርና ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የዓለም ኅብረተሰብ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ በምርጫው ወቅት የውጭ ታዛቢዎች መገኘታቸው ለተገኘው ውጤት የበኩሉን አስተዋጽዖ አድርጓል። ስለሆነም ኅብረቱ ለዓለሙ ኅብረተሰብና ለታዛቢዎቹ ከፍተኛ ምስጋናውን እያቀረበ ለወደፊቱም ከጎናችን እንዳይለዩ በአክብሮት ይጠይቃል።

2.12 በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አንጡራ ሃብትና በጀት የሚንቀሳቀሱት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን (ራዲዮ፥ ቴሌቪዥን፥ ወዘተ...) ዛሬ (በተለይ ከምርጫው በኋላ) ሕዝባችንን በሚያስቆጣ ሁኔታ ለገዥው ፓርቲ ወግነው በማገልገል ላይ ናቸው። ይኸ እጅግ ወገንተኛነት የበዛበት ሁኔታ ባስቸኳይ ቆሞ ሚዛናዊ የሆነ አገልግሎት ለሁሉም ፓርቲዎች እንዲሰጡ ጉባዔው ይጠይቃል።

2.13 ዛሬ ካለው የመንግሥት የመገናኛ ብዙኃን ወገናዊነት የተነሳ ሕዝባችን ለትክክለኛ ኢንፎርሜሽን ጥማት ተጋልጧል፥ በተዛባ ዜናና መረጃ አቅርቦት ለምሬት ተዳርጓል። ይኸንን ጥማቱን በመጠኑም ቢሆን እንደ ጀርመንና የአሜሪካ ድምፅ ወዘተ... ያሉ የውጭ መገናኛ ብዙኃን እያረኩለት ስለሆነ ጉባዔው ለነዚህ ተቋማት ከፍተኛ ምስጋናውን እያቀረበ ለወደፊቱም ከጎናችን እንዳይለዩ ዳግም ጥሪውን ያቀርባል።

2.14 ተቃዋሚው ወገን ከማጣራት ሂደት ያገኘው ነገር ቢኖር የምርጫ ቦርድን ኢሕአዴግአዊነትን ማረጋገጥ ብቻ ነው:: ስለዚህ የምርጫ ማጣራት ጉዳይ ቀደም ሲል ቅንጅቱና ኅብረቱ በጠየቁት መሠረት በገለልተኛ አካል እንዲካሄድ ጉባዔው አበክሮ ይጠይቃል::

2.15 ላለፉት አምስት ዓመታት ይኸ ነው የሚባል ሥራ ሳይሠራ የሥራ ጊዜውን ያጠናቀቀው ፓርላማ የአዲሱን ተተኪ ፓርላማ ሥራ ለማደናቀፍ በችኮላና ብዙ አባላት ባልተገኙበት ሁኔታ ያወጣቸው ሕጎችና ደንቦች በቀጣዩ ፓርላማ ላይ ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸው ተገቢው ሕጋዊ እርምት ባስቸኳይ እንዲወሰድ ጉባዔው ከወዲሁ ያሳስባል::

2.16 የነፃው ፕሬስ ወከባና እንግልት እየደረሰበት ቢሆንም ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ያደረገው አስተዋጽዖ እጅግ ከፍተኛ ነው:: ስለዚህ በነፃው ፕረስ ጋዜጠኞችና ሠራተኞች ላይ የሚደርሰው እንግልትና ወከባ በአስቸኳይ ቆሞ ለአዲሱ ሥርዓት ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ጉባዔው በአንድ ድምፅ ይጠይቃል::

2.17 የኅብረተሰባችን ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶች ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚያደርጉት አስተዋጽዖ እጅግ ከፍተኛና ወሳኝ መሆኑ ይታወቃል:: ስለሆነም ተሳትፎአቸው በሁሉም መስክ እንዲጎለብት ኅብረቱ አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርግ ሆኖ መንግሥት ይኸንን እንዲያግዝና የሚደርስባቸውን ማንኛውንም ፆታዊ ጭቆና እንዲከላከልላቸው ጉባዔው አበክሮ ይጠይቃል::

2.18 ዛሬ አገራችን ባለችበት ፈርጀ-ብዙ ችግሮች ከተለያዩ የዓለም አገራትና ድርጅቶች እርዳታ በየዓይነቱ እየመጣ ለሕዝባችን ይከፋፈላል:: ይሁን እንጅ በማከፋፈሉ ላይ በገዥው ፓርቲ የሚደረገው አድልዖ በተለይ ምርጫው ወዲህ እጅግ የከፋ ሆኖ ኅብረቱ መጥቶ ይስጣችሁ÷ በዬኔ መጥቶ ይስጣችሁ÷ መረራ መጥቶ ያድላችሁ÷ ወዘተ... እየተባለ ለሰብዓዊ እርዳታ የመጣ ቁሳቁስና የአገራችን ገበሬ በገንዘቡ የሚገዛውን ማዳበሪያ እንዳያገኝ እየተደረገ ነው:: ስለዚህ ይኸ አጸያፊ ድርጊት ባስቸኳይ ቆሞ ዕርዳታና ማዳበሪያ ከፖለቲካ ጠቀሜታ ነፃ በሆነ መልክ ለሕዝባችን እንዲታደል ጉባዔው አጥብቆ ይጠይቃል::

2.19 ሕዝባችን ከምርጫው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ሳቢያ የወከባ÷ የድብደባ÷ የንብረት ዘረፋና ሌሎች ተመሳሳይ ወንጀሎች ሲፈጸምበት መቆየቱ ይታወቃል:: በዚሁ ምክንያት አካላቸው የጎደለና ሕይዎታቸውን ያጡ አባሎቻችን በርካታ ናቸው::

በአዲስ አበባና በሌሎች የአገራችን ክፍሎች የሕዝብ ድምፅ እንዲከበር በጠየቁ ሰላማዊ ዜጎች ላይ የተፈጸሙ ዘግናኝ ጭፍጨፋና ግድያዎችን ጉባዔው አጥብቆ ያወግዛል:: ይኸንን ጉዳይ የፈጸሙ ክፍሎች ለሕግ ቀርበው ተገቢው ቅጣት እንዲፈጸምባቸው ኅብረቱ ሲጠይቅ መቆየቱ ይታወሳል:: ይሁን እንጅ እስከዛሬ ድረስ ይኸ ነው የሚባል ሕጋዊ እርምጃ ሲወሰድ አልታየም:: እንዲያውም አንዳንድ ቦታ ጥፋታቸው እንደ ጀብዱ ተቆጥሮ ይሾማሉ ( ለምሳሌ ጀልዱ ምዕራብ ሸዋ)::

ስለዚህ ለጉዳዩ በገዥው ፓርቲና በመንግሥት ትኩረት ተሰጥቶት የተጎዱት ወገኖች ፍትኅ እንዲያገኙ÷ ካሣ ለሚገባቸው ካሣ እንዲከፈላቸው÷ እስር የሚገባቸው አጥፊዎች ለፍርድ ቀርበው በእስራት እንዲቀጡ ጉባዔው አጥብቆ ይጠይቃል::

ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም

አዲስ አበባ

## የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሁለተኛ መደበኛ ጉባዔ የአቋም መግለጫ

ውድ አገራችን ኢትዮጵያ የረዥም ዘመን በድል የተመላ አኩሪ ታሪክ ያላት መሆኑ እንኳንስ እኛ ልጆቿ የዓለም ኅብረተሰብ ያወቀላት ዕውነታ ነው:: ይሁን እንጂ ይኸች በዓለም ሕዝብ ዘንድ አድናቆትና ክብርን የተቸረች አገር አለመታደል ሆኖ ከውስጧ በቅለው ወይ በዘር ሐረግ ወይም በጡንቻና በጠመንጃ ሊገዟት ከወሰኑና ከቆረጡ ልጆቿ ዘንድ ብዙ ጊዜ ይኸንን ዓይነት ከበሬታና አድናቆት ተነፍጋ÷ ሕዝቧ ለመከራና ለሥቃይ ተዳርጎ አገሪቱም የምድር ላይ ገሃነም ሆናባቸው ሲኖሩ ተስተውሏል፤ እየተስተዋለም ነው:: የሩቅ ጊዜውን ትተን በቅርቡ እንኳን ወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ በዚች እናት አገራችን ላይ ያደረሰው እጅግ አሰቃቂ ድርጊት ትልቅ የታሪክ ጠባሳ ሆኖ የሚኖር ነው::

የወታደራዊውን አምባገነን ሥርዓት የተካው የኢሕአዴግ መንግሥት ደግሞ ከድጡ ወደማጡ እንዲሉ አገራችንን ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ወደማትወጣበት አዘቅት ከትቶ ሕዝቧን በዘር÷ በሃይማኖት÷ ወዘተ... እየከፋፈለ በማናከስ ዘመነ ግዛቱን በማራዘም እነሆ ላለፉት አሥራ አምስት ዓመታት በሕዝባችን ጫንቃ ላይ ተቀምጦ የአገራችንንና የጋራ ኅልውናችንን ከፍተኛ አደጋ ላይ ወደሚጥል አቅጣጫ እየወሰዳት ይገኛል::

የግንቦት ወር 1997 ዓ/ም ምርጫ ታሪካዊ ተልዕኮ አገራችን ኢትዮጵያና ሕዝባችን በኃይል÷ በአፈና÷ በሕዝብ መብት ረገጣ አዙሪት ውስጥ ታስረው ለዘመናት ሲዳክሩ ከቆዩበት የመከራ ሰንሰለት ተላቀው ወደ ሰላማዊ÷ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሸጋገሩ የሚደረገውን ትግል የማገዝ ተልዕኮ ነበር:: የኅብረታችን ትግል በዚህ የምርጫ ሂደት ሳቢያ ቀጣይነት ያለው አገር-አቀፍ የሕዝባዊ ትግል ማዕበል በመቀስቀስ መላው ኅብረተሰባችን ወደዚህ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚሸጋገርበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በሚል የተጠነሰሰ ስትራቴጂ ላይ የተገነባ የትግል ስልት ነበር::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህ አገራዊ ጥሪ እንደ አንድ ሰው ሆኖ ከዳር እስከዳር በመንቀሳቀሱ ዛሬ በታሪካችን ከአንድ ትውልድ ወዲህ ያልታየ የትግል ማዕበል አገራችንን አጥለቅልቋት እናያለን:: ይኸ እኛ የሕዝብ ወገኖች የተኩራራንበት÷ መላው ዓለም ያደነቀው የትግል ማዕበል ያለ መስዋዕትነት አልተቀሰቀሰም:: ሕዝባችን ትግሉን እዚህ ታሪካዊ ደረጃ ለማድረስ ከባድ መስዋዕትነት ከፍሏል፤ የዘመናት ግፍና መከራ ባሳሱት ትከሻው ተሸክሞ የደምና የእንባ መስዋዕትነት እየከፈለ እዚህ ደረጃ ያደረሰው ትግል በከንቱ አልነበረም:: በዚች ሉዓላዊት አገርህ ሉዓላዊ መብትህን ተጠቅመህ በምትሰጠው ድምፅ ያለውን ሥርዓት ልትቀይረውና የፈቀድከውን የተሻለ ሥርዓት መገንባት ትችላለህ የሚለውን ዴሞክራሲያዊ መፈክር ተማምኖ በድምፁ ይኸንን መንግሥት እንደማይፈልግ÷ ለውጥ እንደሚሻ÷ ለእኛም÷ ለኢሕአዴግ መሪዎችም÷ ለዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብም ምንም በማያሻማ ሁኔታ አሳይቷል::

ሕዝባችን በግንቦት ሰባት ቀን 1997 ዓ/ም ያሳየው ሥነ ምግባርና ቁርጠኝነት ብልህነቱንና ጨዋነቱን÷ አርቆ አስተዋይነቱንና ብስለቱን ያረጋገጠበት÷ በምሳሌነቱና በታሪካዊነቱ ሲዘከር የሚኖር ነውና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ለሕዝባችን ያለውን አክብሮትና አድናቆት በኩራት ይገልጻል:: በዚህ የወደፊት ብሩኅ ተስፋ ፈንጣቂ የመብት ማስከበር ሰላማዊ ትንንቅ የወደቁ ሰማዕታትን በአክብሮት እንዘክራለን::

ዛሬ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የኢሕአዴግ መንግሥት ሕዝባችንን ባስቆጣ ብቻ ሳይሆን በዓለም-አቀፍ ደረጃም ትዝብት ላይ በጣለው መልክ በገፍና በጠራራ ፀሐይ የሕዝቡን ድል ሰርቆ ህልቆ መሳፍርት መስዋዕት የከፈለው ሰማዕቱ ሕዝባችን ሳይሆን አፋኙ ሥርዓት

በአሸናፊነት ወጥቷል የተባለበት አስቸጋሪ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ እንገኛለን:: የኢትዮጵያ ሕዝብም ድሮውንም ቢሆን ሞቶ ተሰውቶ ያገኘውን ይኸን ድል መልሶ ላለማስነጠቅ ከፈለገ የእስካሁን አይበቃ ይመስል እንደገና እንዲታገል፣ እንደገና እንዲሰዋ፥ ከእንግዲህ ከራሳቸው በስተቀር ማንንም እንወክላለን ብለው ለመግደርደር እንኳን በማይችሉ ጥቂት እብሪተኞች ማስፈራሪያ አዘል ጥሪ እየቀረበለት ነው:: በቅድመ-ምርጫውና በምርጫው ወቅት ለዚህ ድል የተከፈለው መስዋዕትነት ያነሰ ይመስል ይኸንን ድል ላለማስነጠቅ በጀመረው የምርጫ ማግሥት ተጋድሎ እንደገና መስዋዕትነት እየከፈለ ይገኛል:: በሰላማዊ መንገድ ፍትኅ በጠየቁ ልጆቹ ላይ በተፈጸመው አረመኔአዊ ጭፍጨፋ የንፁሃን ደም በገፍ ፈስሷል:: ሆኖም የተፈጸመው ግፍ ጥቂት ፀረ-ሕዝቦች እንደተመኙት የሕዝባችንን ቁርጠኝነት አልበገረውም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪካዊ ድሉን ለማስመዝገብ ሲታገል ባሳየው ወኔ ላይ ዛሬ ደግሞ በገፍ በፈሰሰው የንፁሃን ልጆቹ ደም የተቀሰቀሰው ቁጭትና ቁጣ ተጨምሮበት "ታግላችሁ አታግሉኝ" በሚል ጥሪ የቁርጥ ቀን ልጆች ያለህ የሚል ጩኸቱን የሚያሰማበት የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ እንገኛለን::

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ድሮም ቢሆን ከኢሕአዴግ ፀረ-ሕዝብና ሃላፊነት የጎደላቸው መሪዎች ጋር የሚደረገውን ታሪካዊ ተጋድሎ የቅምጥል ግርግር አድርጎ ቆጥሮት ስለማያውቅ በዚህ ቀውጢ ሰዓት እሱም ከአገራችን የቁርጥ ቀን ልጆች ጎራ ተሰልፎ ለዚህ ሕዝባዊ ኡኡታና ለዚህ አገራዊ ጥሪ የሚያወላውል መልስ ይሰጣል:: የሕዝባችንን ድል ላለማስነጠቅ በሚደረገው ተጋድሎ ከመላው የአገራችን ዴሞክራሲያዊ አገር-ወዳድ ኃይሎች ጎን ተሰልፎ የሚጠበቅበትን የመስዋዕትነት ድርሻ እየከፈለ በግንባር ቀደምነት ወደፊት ለመጓዝ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ዛሬ በሕዝብና በታሪክ ፊት የገባውን ቃል ኪዳን ያድሳል:: ኅብረታችን ይኸንን ቁርጠኛ አቋም ሲወስድ ስለ ቀጣዩ ትግል ምንነት፥ ስለ ዓላማውና ስለ ስልቱ ገና ከወዲሁ ሁሉም እንዲገነዘበው የሚከተሉትን ቁም ነገሮች በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ አስቀምጧል::

ጥቂት የኢሕአዴግ መሪዎች ነጋ ጠባ እንደሚወተውቱት ይኸ ለሕዝብ ድምፅ መከበርና ድል መጠበቅ የሚደረግ ተጋድሎ በጥቂቶች የተጠነሰሰ ሴራ አይደለም:: ትግሉ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ዜጎች ግፊት፥ መስዋዕትነት፥ ፈቃድና ጥያቄ የሚንቀሳቀስ ከጥቂት የሥልጣን ጥመኞች ጋር የሚደረግ ትግል ነው:: ምንም ዓይነት ድብቅነትም ሆነ የጥቂቶች ሴራ ገፅታ የለውም:: ሚሊዮኖች በግልፅና በይፋ በቆሙለት የዴሞክራሲና የብሔራዊ እርቅ ዓላማ፥ ሚሊዮኖች እየሞቱም፥ እየታሰሩም፥ እየተዋከቡም በአደባባይ የሚያራምዱት ከጥቂት በሕዝብ ጀርባ ፀረ-ሕዝብ አጀንዳ ይዘው ከሚንቀሳቀሱ ሴረኞች ጋር የሚካሄድ ትግል ነው::

ጥቂት የኢሕአዴግ መሪዎች ነጋ ጠባ እንደሚለፍፉት ምንም ዓይነት የአመፅም ሆነ የሕገ-ወጥነት ስልት የለውም:: ሚሊዮኖችን ከዳር እስከዳር የሚያንቀሳቅስ ሕዝባዊ ማዕበል በመሆኑ በዚህ ሃያልነቱ ተኩራርቶ የጥቂቶችን የተደራጀ አመፅ በሰላማዊ ክንዱ፥ የራሳቸውን ሕግ የማክበር ፍላጎትም ሆነ ችሎታ ያልታደሉ ጥቂቶችን በሕጋዊ መንገድና ዘዴ ለመቋቋም የተነሳሳ ሰላማዊና ሕጋዊ እንቅስቃሴ ነው::

ጥቂት የኢሕአዴግ መሪዎች እንደሚያስፈራሩት የተያዘው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ኢትዮጵያውያንን ከኢትዮጵያውያን ለማናከስ የሚካሄድ ትግል ፈጽሞ አይደለም:: በትግል ስልት ጉዳይ ብንሄድ እነሱ ከፋፍለው ሊያዳክሙት ሲያሴሩ እኛ ደግሞ ሕዝባችንን ከዳር እስከዳር አስተጋግዘን ለማራመድ የምንዋደቀው፣ በዓላማም ቢሆን እነሱ በጥላቻና በማናከስ በተገነባ ሥርዓት ሲቃዡ እኛ በወንድማማችነት/እህትማማችነት፥ በእኩልነት እጅ ለእጅ ተያይዘን ለምንገነባት የጋራ አገራችን የሚደረግ ትግል ነው::

የተወሰኑ የኢሕአዴግ መሪዎች እንደሚያስፈራሩት የኢትዮጵያ ሕዝብ በማካሄድ ላይ ያለው ተጋድሎ የቂም በቀል መወጫ ግርግር አይደለም:: ኅብረተሰባችን ለዘመናት ፍዳውን ያየበትን የአሸናፊ-ተሸናፊ አስከፊ አዙሪት ለአንዴና ለሁልጊዜ ሰብሮ በፍትኅ፥

በዴሞክራሲና በብሔራዊ እርቅ ላይ የተገነባችና የተረጋጋች ጠንካራና እራሷን የቻለች ሉኣላዊት የጋራ አገር ለመገንባት የሚካሄድ ታሪካዊ ተጋድሎ ነው::

የኢደኃኅ ተጋድሎ ለእነዚህ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ዓላማዎች በሃቅ የቆመ ተጋድሎ ነው:: እነዚህ ዓላማዎች ቀደም ሲል ባሰራጫቸው የፖለቲካ መርኃ-እቅዶቹ (ፕሮግራሞቹ) የሰፈሩ ሲሆኑ ሰላማዊና ሕጋዊ የትግል ስልቱም ከማንም የተሰወረ አይደለም:: የግንቦት 7 ምርጫ ተልዕኮ ቀጣይነት ያለውና አገር-አቀፋዊ የሆነ ሕዝባዊ የትግል ማዕበል ለመቀስቀስና በዚህ ሕዝባዊ ተጋድሎ ተመርኩዞ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ለሚደረገው ትግል ሁኔታዎችን የማመቻቸት ተልዕኮ እንደሆነ በግልፅ ተቀምጧል::

ዛሬ ሕዝባችን ለነዚህ ዓላማዎች ተንቀሳቅሶ አኩሪ ድል ካገኘ በኋላ ድሉ በጥቂት የሥልጣን ጥመኞች እየተነጠቀ ነው:: በመሆኑም ኅብረታችን የሕዝቡ ድምፅ ይከበር በሚለው መፈክር ዙሪያ ተንቀሳቅሶና ከሌሎች ዴሞክራሲያዊና አገር-ወዳድ ኃይሎች ጎን ተሰልፎ የሚጠበቅበትን የትግል ድርሻ ለማበርከት ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ዝግጁ ሆኖ ይገኛል:: ሌላው ዓላማችን ይኸ የሕዝብ ድምፅ በተከበረበት ሁኔታ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ለሚወስደን የሽግግር ዘመን እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልጿል::

ይኸ የሽግግር ዘመን በፖለቲካ ፕሮግራማችን ክፍል ሁለት የተጠቀሱትን የዴሞክራሲ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) እና የብሔራዊ እርቅ ተግባራትን አጠናቀን፥ ሕዝባችን ሚያስፈልገውን ፋታ አግኝቶ በተረጋጋ ኅብረተሰብ ወደ መድብለ-ፓርቲ ምርጫና ሥርዓት የምንሸጋገርበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የምንጠቀምበት ከሌሎች ወገኖች ጋር በመምከር የምናቋቁመው የአጭር ጊዜ ገደብ ያለው የአስተዳደር ዘመን ነው::

ኢዴኃኅ ዴሞክራሲያዊ ሂደቱን ማጎልበት፥ የብሔራዊ እርቅ ሂደትን ፈር ማስያዝ የሚለውን ዓላማ በሃቅ የሚያራምድ፥ አላፊነት የሚሰማው፥ ኢትዮጵያዊ ራዕይ ያለውና ከዚህ ከግንቦቱ ምርጫ ማንም ሆነ ማንም ሳይሆን ኅብረተሰባችንና ዴሞክራሲ በአሸናፊነት ይውጡ በሚለው አቋሙ በሃቅ የሚያምን ድርጅት በመሆኑ፥ በሃቅ የተረጋገጠ የሕዝብ ድምፅ ላይ የተመረኮዘና ሁሉን የሚያካትት የብሔራዊ አንድነት ጊዜአዊ መንግሥት ጥሪ በማድረግ በሕዝብ ድምፅ ለተሸነፈውም ኢሕአዴግ እጁን ዘርግቷል::

የኢሕአዴግ መሪዎች ይኸንን ገንቢ አሳብ ያልሆነ ትርጉም ሰጥተው በድምፅ ስርቆቱና ከብሔራዊ እርቅ ይልቅ ፍጥጫን በሚጋብዝ ፀረ-ሰላምና ፀረ-ሕዝብ አቋማቸው ከፀኑ፤ ኅብረታችን ለነዚህ ዓላማዎች ከሕዝብ ጎን በሃቅ ቆሞ ተጋድሎውን ይቀጥላል፥ ትግሉን ከመሰል ለውጥ ፈላጊና የሕዝብ ወገን ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ይመራል:: ይኸ ተጋድሎ ፍሬ ሰጥቶ ሕዝባችን በገፍ የተሰዋለት የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ዓላማችን እውን እንዲሆን በሚቀጥሉት ወራት ከሚጠብቁት ተግባራት አንፃር የኅብረቱ ጉባዔ በሰፊው ተወያይቶ የሚከተሉትን አቋሞች አንግቦ ለአገራችን ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የትግል አንድነት ጥሪውን አስተላልፏል::

የአገራችን የውድመት አቅጣጫ ያብሰለሰላቸው የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ከተናጠል ትግል የተባበረ ትግል ይሻላል በማለት በሐምሌ ወር 1995 ዓ.ም በአሜሪካ፥ በሜሪላንድ ክፍለ አገር በሮክ ቪል ከተማ ተሰባስበው ሰፊና ጥልቅ ውይይት ካካሄዱ በኋላ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን (ኢዴኃኅን) በመመሥረት የተባበረ ትግላቸውን መቀጠላቸው ይታወሳል::

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ሐምሌ 16 ቀን 1995 ዓ/ም መመሥረት የጋራና የተቀናጀ ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብን የመብትና የእኩልነት ትግል ላይ የዓይነትና የይዘት ለውጥ እንዳስገኘ፥ በአገራችን የፖለቲካ ሕይዎት ላይ መሰል የሌለው አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንዳበረከተና ገዥውን ፓርቲም ለመጀመሪያ ጊዜ በሕዝቡ ትግል መልክ መያዝ ተቃዋሚው ክፍል በሚያቀርባቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት ለመስጠት እንዳስገደደው ግልጽ ነው።

የኅብረቱ አባል ድርጅቶች በዚሁ ጉባዔአቸው የመሠረቱት ሸንጎም ዓመታዊ ስብሰባዎችን በማካሄድ፥ የኅብረቱን ድርጅታዊ ይዞታ እየመረመረ፥ የውጪውንና የአገር ውስጡን ትግል የሚያግዙ መመሪያዎችን በማውጣት የሕዝባችንን ትግል ወደፊት በማራመድ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፥ እያደረገም ነው።

በዚሁ መሠረት የኢዴኃኅ ብሔራዊ ምክር ቤት/ሸንጎ/ ሁለተኛ መደበኛ ጉባዔውን ከነሐሴ ፲፬ ቀን እስከ ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. በሮክቪል ሜሪላንድ ዩ.ኤስ. ኤ አካሂዷል።

ይኸው ዓመታዊ ጉባዔ ቀደም ሲል በተዘጋጁና በኋላም በውይይት በፀደቁ የመወያያ ርዕሶች/አጀንዳዎች/ ላይ በዝርዝር፥ በስፋትና በጥልቀት ተወያይቶ ግንዛቤዎችን ወስዷል፥ ውሳኔዎችንም አሳልፏል። ኅብረቱ ባለፈው አንድ ዓመት በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ያከናወናቸውን ተግባሮች፥ ያስመዘገባቸውን ውጤቶችና የገጠሙትን ችግሮች የሚያካትቱ ከጽ/ቤቶቹ፥ ከኅብረቱ የተግባር ኮሚቴዎችና ከቁጥጥር/ኦዲት/ እና ኢንስፔክሽን ኮሚቴዎች ዘገባዎች ቀርበውለት ጉባዔው ሰፊ ውይይት በማካሄድ ዘገባዎችን አጽድቋል።

የቀረቡ ዘገባዎች አጠቃላይ ይዘታቸውም እንደሚከተለው ነበር።-

1. የኅብረቱ የውስጥ ድርጅታዊ ይዘት አቅም፥ ጥንካሬና ድክመቶች፤
2. ኅብረቱ ባለፈው ዓመት (፲፱፻፺፯ ዓ.ም.) ልዩ ጉባዔውን ካካሄደ ወዲህ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ስለተደረጉ እንቅስቃሴዎች፤
3.. የኅብረቱን ዋና ጽ/ቤትና የውጭ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፥ የኅብረቱን ድርጅታዊ ይዘትና አቅም ለማጠናከር ስለተደረጉ ጥረቶች፤
4. ምርጫውን ነፃና ርቱዓዊ ለማድረግ ከገዥው ፓርቲና መንግሥት ጋር ስለተደረጉ የድርድር ጥረቶች፤
5. ኢዴኃኅ የአገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በአገር ውስጥ በግልጽ በሚንቀሳቀሱ የኅብረቱ አምስት አባል ድርጅቶች ዋቢነት (አማካይነት) ሕጋዊ ሆኖ ስለመመዝገቡ፤
6. የግንቦት ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ምርጫን ነፃና ርቱዓዊ ለማድረግ በአገር ውስጥና በውጭ አገሮች ስለተደረጉ ጥረቶችና ሙከራዎች፤
7. የኅብረቱ የአመራር አባላትና አካላት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመብቱ የሚያደርገው ትግል በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል በተለይም በነፃና ርቱአዊ ምርጫ ዙሪያ የጠራ ግንዛቤ እንዲኖረው በአገሪቱ ውስጥ ስለተደረገው ጥረት፤
8. በውጭ አገራትና ክፍለ-ዓለማት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ጉዳይ ተሳታፊ እንዲሆኑና በድጋፍ አካሎች አማካይነት በተደራጀ መልክ እንዲንቀሳቀሱ ስለተደረጉ ጥረቶችና ውጤቶች፤
9. የእናት አገራችንን የወቅቱ ጉዳይ የውጭው ዓለም እንዲገነዘብና ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ድጋፎች እንዲገኙ ስለ ተደረጉ ጥረቶች፤
10. በግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. በአገራችን የተካሄደውንና በዓይነትም ሆነ በይዘት ቀደም ሲል ከተደረጉ ምርጫዎች ሁሉ ለየት ያለና ሕዝባዊ ነውጥ ያሳየውን አጠቃላይ የምርጫ ሂደት፤
11. ስለምርጫው ክንዋኔና ውጤት፤

12. ከምርጫው ወዲህ በገዥው ፓርቲ፥ በመንግሥትና በምርጫ ቦርድ ስለተወሰዱና እየተወሰዱ ስላሉ የሕዝብ ድምፅ ስርቆት፥ አፈናዎችና አጠቃላይ ችግሮች፤
13. ኢዴኃኅ ከመንግሥት ጋር የምርጫውን ሜዳ ለማስተካከል ያካሄደው እልህ አስጨራሽ ጥረት በሌሎች ተቀዋሚ ክፍሎች ባለመደገፉ ይኸ ጥረት የተፈለገውን ውጤት ስላለማስገኘቱ፤
14. በግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ምርጫ ሂደትና ከዚያም ወዲህ ባለው ሁኔታ ላይ ስለነበረው የውጭ ታዛቢዎች ሚናና ተግባር፤
15. ትግሉን ለማጎልበት ኅብረቱ ከሌሎች ድርጅቶች የፖለቲካ፥ የሞያና፥ የሲቪክ ድርጅቶችና ስብስቦች ጋር ስላደረጋቸው የሥራ ግንኙነቶች፤
16. ኢዴኃኅ ለ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. አገር አቀፉ ምርጫ ለመንግሥት ስላቀረባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ስለተገኙ ውጤቶች፤
17. ኢዴኃኅ ባለፈው አንድ ዓመት ስላስመዘገባቸው አጠቃላይ አኩሪ ድሎች፤
18. ከላይ በተራ ቁጥር 16 በተጠቀሰው ምክንያት ኢዴኃኅ ወደ ምርጫው ገብቶ ሙሉ ለሙሉ ለመሳተፍ የወሰነው በጣም ዘግይቶ ስለመሆኑና እንዲሁም በአሠራር በኩል በነበሩ አንዳንድ ጉድለቶች ምክንያት የሚጠበቀውንና ሊያመጣ ይችል የነበረውን አገር-አቀፍ የምርጫ ውጤት ስላለማግኘቱ ጉባዔው ተገቢውን ግንዛቤ ከጨበጠ በኋላ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፏል::

<u>ውሳኔዎች፤</u>

1. የግንቦት ሰባት ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ምርጫ ውጤት በኢሕአዴግና በምርጫ ቦርድ መመሳጠር በተጭበረበረትና የሕዝብ ድምፅ ያለ አንዳች ሀፍረት በገፍ በተሰረቀበት ሁኔታ፥ እንዲሁም የምርጫውን ጉድለት/ election irregularities/ የማጣራቱ ሂደት በኢሕአዴግና በምርጫ ቦርዱ ከሰኔ ሦስቱ የሦስትዮሽ ስምምነት ውጭ በተወሰዱ እርምጃዎች በተኮላሸበት ሁኔታ የገዥውን ፓርቲ አሸናፊነት ምርጫ ቦርዱ ማወጁን ጉባዔው በጥብቅ ያወግዛል::

2. የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኸንን ሸፍጥ አልተቀበለውም፤ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትም ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደገለፀው ሁሉ አሁንም አይቀበለውም::

3. ኅብረታችን በከባድ መስዋእትነት የተገኘውን የሕዝብ ድል ለማስከበር በሚደረገው ሰላማዊ የመብት ትግል ከመሰል ለለውጥ የቆሙ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር በመሆን በግንባር ቀደምትነት ትግሉን ለማስተባበርና ለመምራት ያለውን ቁርጠኛነት እያረጋገጠ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ለዴሞክራሲያዊ ለውጥና ለሕዝብ መብት መከበር የቆሙ የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የአገራችን ዴሞክራቶች፥ የሲቪክ ማኅበረሰቡ አባላት፥ የሙያ፥ የሠራተኞች፥ የገበሬዎች፥ የወጣቶች፥ የተማሪዎች፥ የሴቶችና የሌሎች ስብሰቦች ለዚህ ሰላማዊና ሕጋዊ ትግል ከጎኑ እንዲቆሙ ጥሪ ያቀርባል::

4. በአገራችን የተጀመረውን የዴሞክራሲ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) ለማገዝ ሲሉ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ የተንቀሳቀሱ የአገሪቱ ዜጎች በሰበብ አስባቡ ይታሠራሉ፥ ይዋከባሉ፥ ከቀያቸው ይባረራሉ፥ ይባስ ሲልም ይገደላሉ:: ይኸ ላለፉት ፲፭ ዓመታት ሲካሄድ የቆየው የኢሕአዴግ ቀጣይና የተሰላ የግፍ ድርጊት ባስቸኳይ ቆሞ ዜጎቻችን ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው ተከብሮ በአገራቸው በሰላም እንዲኖሩ እንዲደረግ፥ የፖለቲካ እስረኞችም እንዲፈቱ ጉባዔው አጥብቆ ይጠይቃል::

5. ከግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ምርጫ በተያያዘ ዛሬ ከላይ በተራ ቁጥር 4 የተጠቀሰው ተግባር አይሎ የቀጠለ ሲሆን ዜጎቻችን በጥይትየተደበደቡ ተገድለዋል፥ ከቀያቸው ተሰደዋል፥ እየተሰደዱም እየታሠሩም ነው። ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን ተጠቅመው ለሕዝብ ድምፅ መከበር ጥያቄአቸውን በሰላማዊ መንገድ ስላቀረቡ ብቻ በግፍ የተገደሉ፥ የተጎዱና የተንገላቱ ንፁህ ዜጎችን ጉዳይ የሚያጣራ ልዩ፥ ገለልተኛና የዓለም-አቀፉን የሰው ልጆች መብት ተከራካሪዎችና ተቋማት ያካተተ አንድ አካል በአስቸኳይ እንዲቋቋም ጉባዔው አጥብቆ ይጠይቃል።

6. ከምርጫው ጋር በተያያዘ የታሠሩ ዜጎቻችን ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ ባስቸኳይ ተፈትተው ለተገደሉት ዜጎቻችን ቤተሰቦች የደም ካሣ ተከፍሎ ገዳዮችም ለፍርድ እንዲቀርቡ፥ ከቀያቸው የተባረሩ/ የተሰደዱ ወደቀያቸው እንዲመለሱ፥ ንብረታቸው ለተዘረፈና ለወደመ ዜጎች አስፈላጊው ካሣ እንዲከፈላቸው ጉባዔው ይጠይቃል።

7. የምርጫውን ውጤት የማጣራት ሂደት ኢሕአዴግና የምርጫ ቦርዱ ከስምምነት ውጭ በወሰዷቸው እርምጃዎች ምክንያት በመኮላሸቱ የተፈጠረውን ውጥረት ለመፍታት በኢዴፓን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወዳዳሪዎች ጉባዔ በተወሰነው መሠረት የምርጫው አጠቃላይ ሂደትና ውጤት በሌላ ሁሉም ወገኖች በሚስማሙበትና ተኣማኒነት ባለው ገለልተኛ አካል እንዲመረመር፥ እንዲገመገምና ፍትኃዊ እልባት እንዲያገኝ፥ ውጤቱም ባስቸኳይ ለሕዝባችን እንዲገለጥ ጉባዔው አበክሮ ይጠይቃል።

8. የሕዝባችንን ድል ሳናስነጥቅ ለአገራችንና ለሕዝባችን ሰላምና ደኅንነት፥ ለዴሞክራሲያዊ ሂደት መጎልበት፥ በብሔራዊ እርቅ ላይ የተገነባ የተረጋጋ ኅብረተሰብን መሠረት ለመጣልና የመልካም አስተዳደር ሥርዓትን ለመዘርጋት ለሚያስፈልገን የሽግግር ዘመን ቀደም ብሎ በኅብረቱ በቀረበው አሳብ መሠረት የብሔራዊ አንድነት መንግሥት መቋቋምን ጥያቄ ገዥው ፓርቲ (ኢሕአዴግ) ተቀብሎ ለተግባራዊነቱ የጋራ እንቅስቃሴ እንዲጀመር፥ ለዚህ ተግባራዊነትም መላው ሕዝባችንና የዓለም ሰላም ወዳድና ለዴሞክራሲ የቆሙ መንግሥታትና ኃይሎች አስፈላጊውን ጫና እንዲያደርጉ ጉባዔው በአንክሮ ይጠይቃል።

9. እነዚህ በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት የቀረቡ ገንቢና ዴሞክራሲያዊ አሳቦች በኢሕአዴግ በኩል ተቀባይነት ካላገኙና ገዥው ፓርቲ በተያያዘው ሃላፊነት የጎደለው አቋምና በማጭበርበር አድራጎቱ ገፍቶ የብሔራዊ እርቁን አሳብ አሻፈረኝ የሚል ከሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ለለውጥ የቆሙ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች፥ የሲቪክ ማኅብረሰቦች፥ የሠራተኞች፥ የገበሬዎች፥ የወጣቶች፥

የተማሪዎች፥ የሴቶችና ሌሎች ሕዝባዊና የሙያ ድርጅቶች በሕገ መንግሥቱ

ማዕቀፍ ውስጥ ያሉትን የሰለማዊና የሕጋዊ የትግል ስልቶች በመጠቀም በአንድነት እንዲሰለፉና በጋራ እንዲንቀሰቃሱ ጉበዔው ጥሪውን ያቀርባል።

10. ኅብረቱ ያቀረባቸውን የዴሞክራሲ ዓላማዎችና ገንቢ አሳቦች ለማራመድና ተግባራዊ ለማድረግ ከኢሕአዴግ ጋር የሚደረገው ትግል ፍሬያማ እንዲሆንና ተፈላጊውን አዎንታዊ ውጤት እንዲያስገኝ ትግሉ የጠቅላላው ሕዝባችን ሰፊና አገር-አቀፍ ዴሞክራሲያዊ የጋራ እንቅስቃሴ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ ጋር

በተያያዘ ማንኛውም በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ከኢሕአዴግ ጋር የሚደረግ ድርድር

ሕዝቡን የሚያሳትፍና በትግሉም የታጀበ መሆን ይኖርበታል ይኸ የጠቅላላው ኅብረተሰባችን የዴሞክራሲ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) እና የብሔራዊ እርቅ ትግል በተደራጀና በተቀናጀ መልክ መካሄድ አለበት፡፡ ስለሆነም የአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶችን፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት፥ የሠራተኞች፥ የገበሬዎች፥ የወጣቶች፥ የሴቶች፥ የተማሪዎች፥ የሐይማኖት ድርጅቶች፥ ወዘተ... ተወካዮች የሚሳተፉበት አንድ “ የሰላም፥ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ አገር-አቀፍ ጉባዔ ” ለመስከረም 20 እና 21 ቀን 1998 ዓ/ም አዲስ አበባ እንዲጠራ ጉባዔው ወስነኗል፡፡

11. የአገር አቀፉን ጉባዔ ጥሪ ተግባራዊ የሚያደርግ አንድ ሁሉን-አቀፍ ግብረ ኃይል አሳቡን ከሚደግፉ ወገኖች ጋር ኅብረቱ በአስቸኳይ እንዲያቋቁም ጉባዔው ወስኗል፡፡ መመሪያም ሰጥቷል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ለሚመለከታቸው ወገኖች ጉባዔው የትብብር ጥሪ ያቀርባል፡፡

12. ሕዝባችን ከድህነት፥ ከበሽታና ከሰቆቃ ተላቆ፥ ፍትኅ፥ ዴሞክራሲ፥ ሰላምና ብልጽግና በሰፈነባት አገር በሰላም እንዲኖር ለማድረግ የተያያዝነውን የመብት ማስከበር ትግል እንዲረዱ ጉባዔው ያፀደቃቸውን አሳቦችና የትግል ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ ለሚያስፈልገው ቀጣይ ትግል ሕዝባችን ያለውን ድጋፍ እንዲገልጽ ከአዲስ አበባ ጀምሮ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎችና በዓለም-አቀፍ ደረጃ መስከረም 22 ቀን 1998 ዓ/ም (October 2, 2005) “ የሰላም፥ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ” ሰላማዊ የድጋፍ ሰልፍ እንዲዘጋጅና ተግባራዊ እንዲሆን ተወስኗል፡፡ ይኸ የጋራ ዓላማ ዕውን እንዲሆን በውጭም በውስጥም የሚገኘው ወገናችን ሁሉ ልዩ ትኩትረት በመስጠት በገንዘብም ሆነ በአስፈላጊው ሁሉ ትብብሩን እንዲገልጽ ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን፡፡

13. ዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ የጉዳዩ ባለቤት በሆኑት የኢትዮጵያ ሕዝብና በተቃዋሚ ኃይሎች ጉትጎታ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው አስቸጋሪና እጅግ አስጊ የፖለቲካ ሁኔታ ይበልጥ እንዲያውቅ እየተደረገ ቢቆይም፥ ትላልቅና ኃያላን መንግሥታት በተናጠልም ሆነ በአህጉራዊ ማኅበሮቻቸው አማካይነት በሦስተኛው ዓለም አገሮች ውስጥም ጭምር ስለዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች መስፈን አስፈላጊነትና ስለመልካም አስተዳደር፥ ስለሰብአዊ መብቶች መከበር የሚቆረቆሩና የሚከታተሉም መሆናቸውን በመገንዘብ፥ ኢትዮጵያ ውስጥም ይኸንኑ ቃላቸውን እንዲያከብሩ በጥብቅ እየተጠየቁ እንደነበር ይታወቃል፡፡ በግንቦቱ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ምርጫ መንግሥታቱ በሚልኳቸው የምርጫ ታዛቢዎች አማካይነት ቅድመ ምርጫ ሁኔታዎችንና የምርጫውን ሂደት (ውስን በሆኑ አካባቢዎች ቢሆንም) እንዲሁም ድኅረ ምርጫ ክስተቶችን፤- የድምፅ ቆጠራ መቋረጥን፥ ወከባን በኢሕአዴግ የተጫነውን ሕገ-ወጥ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፥ ተቃውሞ ባሰሙ ሰለማዊ ሰልፈኞች ላይ የተፈፀመውን ግድያ፥ እስራት፥ በጉልበተኛው ገዥ ፓርቲና በተቃዋሚዎች መካከል የተፈጠሩትን ውዝግቦችና ንትርኮች ወዘተ... ለመታዘብ ያደረጉትን ጥረት ኢዴኃኅ አዎንታዊና አልፎ አልፎም አበረታች እንደነበር ተገንዝቧል፡፡ ሆኖም ግን ከትላልቅ መንግሥታት መሃል በተለይ የተወሰኑት በጨዋነትና በአስደናቂ ሥነ ምግባር ተመርቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነቱን ለማረጋገጥ የሰጠውን ድምፅ በሌላ አነጋገር የሥልጣን ባለቤትነት መብቱን በአምባገነን ገዥዎቹ ሲነጠቅ ከበዳዮቹ ጋር ተባባሪ ሊያሰኛቸው በሚችል ደረጃ የኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍና አጋርነት የማግሸሽ ዝንባሌ በማሳየታቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ ላይ የነበረው ግምትና አመኔታ እንዲኮስስ ሆኗል፡፡ በዚህ አዝማሚያም ጉባዔው አዝኗል፡፡

ለሃቅ በጽናት ለቆሙት ክፍሎች አክብሮቱን ይገልጻል:: አሁንም ዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ በተለይም ኃያላኑ መንግሥታት በቅርቡ ስለ ሦስተኛ ዓለም አገሮች ድህነት ቅነሳና ብድር ስረዛ በስኮትላንድ ባደረጉት ስብሰባቸው ላይ በሕዝብ ዘንድ አመኔታን ያተረፈ መልካም አስተዳደር መኖርን አስፈላጊነት በገለፁት መሠረት ከአምባገነኖች ጋር ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማስፈን፥ መልካም አስተዳደር ለመመሥረት፥ ለፍትሕና የነፃ ዳኝነት ሥርዓት መኖርና ለዜጎች መሠረታዊ መብት መከበር ከሚታገለው የኢትዮጵያ ሕዝብና ከመሪ ድርጅቶቹ ከኢዴኃኅና ሌሎችም ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር እንዲቆሙና እንዲተባበሩ ጉባዔው በአክብሮት ይጠይቃል::

14. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ከአገሪቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሆነ ከአገር ወዳዶች ጋር በመሆን የዚችን አገር የወደፊት ዕጣ ፈንታ ለመወሰን ያደረገውና የሚያደርገው ጥረት አመርቂ መሆኑን ጉባዔው ተገንዝቧል:: አሁንም ከሌሎች ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ፥ የሲቪክና የሙያ ድርጅቶች ጋር የሚኖረውን የትግል ትስስር የጋራ ትግሉን በሚያጎለብትና አገርን በሚጠቅም መልክ እንዲቀጥልበት ጉባዔው ወስኗል::

15. በውጭው ዓለም የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ከመቸውም ይበልጥ በአገሩ ላይ ጉዳይ የሚያደርገውን ቀጥታ ተሳትፎና አስተዋፅዖ እያደነቀ፥ ይኸ እንቅስቃሴ ለቀጣይ ትግሉ በሚጠቅም መልክ የወገናችን የትግል ትስስር እንዲዳብር ኅብረቱ የሚቻለውን ሁሉ እንዲያደርግ መመሪያ ሰጥቷል:: የኅብረቱ የድጋፍ አካላት ላደረጉት አኩሪ ሁለ-ገብ ድጋፍ ጉባዔው ምስጋናውን በአድናቆት ገልጿል:: ወደፊትም የበለጠ ጥረት እንደሚያደርጉ ያለውን ዕምነት ይገልጻል::

16. በአገሪቱ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በግልም ሆነ በቡድን በአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ለማስገኘት በሚደረገው ትግል መሳተፉ ለአገራችን ሁለንተናዊ እድገት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ አጠያያዊ አይደለም ከዚህ አኳያ ዛሬ በርካታ የአገራችን ልጆች ለረዥም ዓመታት ያካበቱትን ፈርጀ ብዙ ልምድ ለአገራቸው እድገትና ለዜጎቿ ብልጽግና ማዋል ሲችሉ በኢሕአዴግ በጠላትነት ተፈርጀው ከአገራቸው ውጪ ይገኛሉ:: ይኸ ለአገራችን ጉዳት እንጂ ያስገኘው አንዳችም ጠቀሜታ የለም:: ስለሆነም በዚህ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰቦች ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው ተጠብቆላቸው ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ አገር ውስጥ ገብተው የበኩላቸውን ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ የተጣለባቸው ዕገዳ እንዲነሳ ጉባዔው አጥብቆ ይጠይቃል:

**የሕዝብ መብት ይከበር!!!**
**የተነጠቀ የሕዝብ ድምፅ ይመለስ!!!**
**የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት መብቱን ያስከብራል!!!**
**በአምባገነኖች የሚገፋው የጥፋት አዙሪት ይሰበር!!!**
**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

**ዋሽንግተን ዲ.ሲ. አሜሪካ**
**ነሐሴ ፱ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም**
**(August 22, 2005)**